ARLINGTON VIRGINIA Public Health

# ካምፒሎባክቴሪዮሲስ (CAMPYLOBACTERIOSIS)

10/31/2023

## ፋይረሱ/ኢንፌክሽኑ ምንድን ነው?

ካምፒሎባክቴሪዮሲስ (Campylobacteriosis) *ካምፒሎባክተር (Campylobacter) ተብሎ በሚጠራ ባክቴሪያ ምክንያት የሚመጣ ኢንፌክሽን ነው።* ካምፒሎባክተር (Campylobacter) በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ እጅግ ከተለመዱ የተቅማጥ መንስኤዎች መካከል አንዱ ነው።

## ማንን ይይዛል?

ማንም ሰው በካምፒሎባክቴሪዮሲስ (Campylobacteriosis) ሊያዝ ይችላል። ጨቅላ ህጻናት፣ ህጻናት እና የሰውነት የበሽታ መከላከል ስርአታቸው የተዳከመ ሰዎች የበለጠ በጣም የመታመም እድል አላቸው።

## ቫይረሱ እንዴት ይዛመታል?

አንድ ሰው በካምፒሎባክተር (Campylobacter) የተበከለ ምግብ ወይም መጠጥ ከበላ ወይም ከጠጣ ሊታመም ይችላል። አንድ ሰው ለመታመም እንደ አንድ ጠብታ ጥሬ የዶሮ ጁስ ያሉ ጥቂት ባክቴሪያዎችን ብቻ መውሰድ በቂው ነው።

አንድ ሰው በሚከተለው ምክንያት ሊታመም ይችላል:

- ጥሬ ወይም በደንብ ያልበሰለ ስጋ በተለይም የዶሮ ስጋ ከበላ
- እንደ የቆሸሸ መክተፊያ ካለ እቃ ላይ የተበከለ ምግብ ከበላ
- ያልፈላ (ጥሬ) ወተት ወይም የተበከለ ውሃ ከጠጣ
- እንስሳትን ከነካ በኋላ እጆቹን ካልታጠበ
- በካምፒሎባክቴሪዮሲስ (Campylobacteriosis) በተያዘ ሰው ሽንት ቤት ከተጠቀመ በኋላ እጆቹን በአግባቡ ሳይታጠብ የተዘጋጀ ምግብ ከበላ

## ምልክቶች ምን ምንድን ናቸው?

- ብዙውን ጊዜ የደም መቀላቀል ምልክቶች ያሉት ከመለስተኛ እስከ ከባድ ተቅማጥ
- ትኩሳት
- የሆድ ቁርጠት
- ማቅለሽለሽ እና ማስመለስ
- አንዳንድ ሰዎች ምንም ምልክቶች አይታዩባቸውም።

ምልክቶቹ በአብዛኛው ለባክቴሪያው ከመጋለጥ በኋለ ካሉት ከ2–5 ቀናት ውስጥ የሚጀምሩ ሲሆን በአንድ ሳምንት ያክል ጊዜ ውስጥ ይጠፋሉ።

## የሚመረመረው እንዴት ነው?

የላብራቶሪ ምርመራዎች ካምፒሎባክተር (Campylobacter) ን በሰገራ (አይነ ምድር)፣ የሰውነት ቲሹ ወይም ፈሳሾች ውስጥ ሊያገኙ ይችላሉ።

## ህክምናው ምንድን ነው?

ብዙ ሰዎች ለመዳን መድሃኒት አያስፈልጋቸውም። ሰዎች የሰውነት ውስጥ ፈሳሻቸውን ለመጠበቅ ፈሳሽ መጠጣት አለባቸው። ከባድ ህመም ያለባቸው ወይም በከባድ ህመም የመታመም ስጋት ያለባቸው ሰዎች አንቲባዮቲክስ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። አንድ ሰው አንቲባዮቲክስ የሚያስፈልገው ስለመሆኑ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ይወስናል።

## እንዴት መከላከል ይቻላል?

- በተለይም በሚከተሉት ሁኔታዎች እጆችን በተደጋጋሚ በሳሙናና ውሀ ቢያንስ ለ20 ሴኮንዶች መታጠብ፡
  - ሽንት ቤት ከመጠቀም ወይም ዳይፐር ከመቀየር በኋላ
  - ምግብ ከመንካት በፊት እና በኋላ
  - እንስሳትን ከመንካት በኋላ
- ጥሬ የዶሮ ስጋን ከሌሎች ምግቦች ለይተው ለብቻው ያስቀምጡ
- ምግብን በትክክለኛው የሙቀት መጠን - ለዶሮ ቢያንስ 165 °F ማብሰል (የሙቀት መጠኖችን ለማረጋገጥ የምግብ ሙቀት መለኪያ ይጠቀሙ)
- ያልተፈጨ (ጥሬ) ወተት ወይም ጭማቂ ወይም አደገኛ ሊሆን የሚችል ውሃ አይጠጡ (ለምሳሌ፣ ከኩሬ፣ ከሐይቆች ወይም ከመዋኛ ገንዳዎች የሚወጣ ውሃ)

## አንድ ሰው ቫይረሱን የሚያስተላልፈው ለምን ያክል ጊዜ ነው?

ሰዎች ምልክቶቻቸው ከቆሙላቸው ከጥቂት ቀናት እስከ ብዙ ሳምንታት ካምፒሎባክቴሮሲስ (Campylobacteriosis) ን ማስተላለፍ ይችላሉ።

## አንድ ሰው ምን ያክል ጊዜ በቤት ውስጥ መሆን አለበት?

ተቅማጥ የያዘው ሰው ተቅማጡ እስኪቆምለት ድረስ በቤት ውስጥ መቆየት አለበት።

## ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የምችለው እንዴት ነው?

- ስለ ካምፒሎባክቴሮሲስ (Campylobacteriosis) ለተመለከቱ ጉዳዮች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።
- ስለ ምግብ ወለድ ህመም ለተመለከቱ ጥያቄዎች የአርሊንግተን ካውንቲ የማህበረሰብ ጤና የተላላፊ በሽታ ፕሮግራም ድረገጽን በ (https://www.arlingtonva.us/Government/Programs/Health/Public-Health/Communicable-Disease-Programs) ይጎብኙ።
- የተጠረጠረ ምግብ ወለድ ህመምን ሪፖርት ለማድረግ የMy Meal Detective ድረገጽን በ (https://redcap.vdh.virginia.gov/redcap/surveys/?s=PJACE4A4EY) ይጎብኙ።
- ስለ *ካምፒሎባክተር (Campylobacter)* በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የCDCን ድረገጽ በ (https://www.cdc.gov/campylobacter) ይጎብኙ።

ARLINGTON VIRGINIA
Public Health
2100 Washington Boulevard
Arlington, VA 22204
ወደዚህ ቁጥር ይደውሉ 703-228-5200፣ አማራጭ #1፣ እና የእለቱን ነርስ ይጠይቁ
www.arlingtonva.us